# መጽሐፈ ሩት

ይህ መጽሐፍ በመሳፍንት ዘመን የተፈጸመን ውብ የሆነ ታሪክ የሚገልጽ ሲሆን በመጽሐፈ መሳፍንት ያየነውን አሳዛኝና ከኃጢያት ጋር የመደራደር ታሪክ ተቃራኒ የሆነ፤ አንዲት ሞዓባዊት የሆነች ሩት የምትባል አሕዛብ እንዴት አማልክትዋንና አገርዋን ትታ የእስራኤልን አምላክ ፍለጋ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እንዴት እንደተቀላቀለችና በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ የሆነ የክብር ስፍራን እንዳገኘች የሚተርክ መጽሐፍ ነው፡፡

<u>በመጽሐፈ መሳፍንት</u> የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑ እስራኤላውያን በተደጋጋሚ እግዚአብሔር አምላካቸውንና ያደረገላቸውን ውለታ ረስተው እንዴት ከአሕዛብ ጋር እንደተቀላቀሉና የአሕዛብን አማልክት ያመልኩ እንደነበረ ይተርካል፡፡

<u>በመጽሐፈ ሩት</u> ደግሞ፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ካልሆነ ወገን የነበረች አንዲት ሞዓባዊት (ሩት) እንዴት አገርዋን፣ ሕዝቧንና አማልክትዋን ትታ ወደ እስራኤል አምላክና ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ እንደመጣች ይተርካል፡፡

ይህንን መጽሐፍ ማን እንደጻፈው ባይታወቅም እንደ መጽሐፈ መሳፍንት ሳሙኤል ሳይጽፈው አይቀርም ተብሎ ይገመታል፡፡

የተጻፈበት ዘመን በዳዊት ዘመን እንደሆነ ይገመታል ይህንንም የሚያመለክተው ሐሳብ በምዕ 4:21-22 ላይ የሩትን ዘር ሲዘረዝር እስከ ዳዊት ድረስ ይሄድና ያቆማል፡፡ ሩት የዳዊት ቅድመ አያት እንደሆነች ይገልጻል፡፡ ስለዚህ ከዳዊት ዘመን በፊት መጽሐፉ ሊጻፍ አይችልም፡፡ በመሳፍንት ዘመን እንዳልተጻፈ የሚያሳየው ሌላው ማስረጃ በምዕ 1:1 ላይ «መሳፍንት ይፈርዱ በነበረ ጊዜ» በማለት የመሳፍንትን ዘመን በኃላፊ ጊዜ ነው የሚያመለክተን፡፡

ይህ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሴት ስም ከተሰየሙት ሁለት መጽሐፍት አንደኛው ነው ሁለተኛው መጽሐፍ መጽሐፈ አስቴር ነው።

ይህንን መጽሐፍ ጥሩ አድርጎ የሚገልጽልን የአዲስ ኪዳን ጥቅስ አለ፤

«ጴጥሮስም አፉን ከፍቶ እንዲህ አለ:- እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያዳላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደሆነ በእውነት አስተዋልሁ» (ሐዋ 10:34-35) ጴጥሮስ፣ በዚህ ክፍል የሚናገረው ቆርኔሌዎስ ስለሚባለው እግዚአብሔርን ይፈራና ያመልክ ስለነበር አሕዛብ ነው። እግዚአብሔርም ይህንን ሰው አክብሮ ከአሕዛብ መካከል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገባበትን ዕውነት ሲገልጽለት እናያለን።

ሩትም እንደዚህ ዓይነት እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ስለነበረች እንዴት እግዚአብሔር እንዳከበራት የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። የንጉሥ ዳዊት ቅድመ አያት መሆንዋ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስም የመጣበት የዘር ሐረግ በእርስዋ በኩል እንደሆነ እናያለን። «ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ፤ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና» (ዕብ 11:6) ይህች ከአሕዛብ ወገን የሆነች ሴትም እግዚአብሔርን ፈልጋ ከእግዚአብሔር ዋጋ እንደተቀበለች እንገነዘባለን።

መጽሐፈ ሩት አራት ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ ልዩ ትኩረት አለው።

## መጽሐፉ በአራት ይከፈላል።

1) የሩት ታማኝነት፣ እምነትና፣ ፍቅር (ምዕ. 1)
2) የሩት ትጋትና ትሕትና (ምዕ. 2)
3) የሩት ታዛዥነት (ምዕ. 3)
4) የሩት ደሞዝና ዋጋ (ምዕ. 4)

# የሩት አስደናቂ ታማኝነትና ፍቅር (ሩት ምዕ. 1)

ምናልባት ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኛ ለሆንነው ለሰው ልጆች ራሱን በመስጠት ካሳየው ፍቅር ቀጥሎ የሚያስደንቅ ፍቅርን በሩት ሕይወት እናያለን።

ታሪኩ የሚጀምረው በቤተልሔም ከተማ ነው። በዚህ አገር ራብ በመጣ ጊዜ አንድ አቤሜሌክ የሚባል ሰው ኑኃሚን ከምትባል ሚስቱና ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ረሃብ ለመሸሽ ወደ ሞዓብ ምድር ሄዱ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንደምናየው ረሃብ የሚመጣው የእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ በሚያምጹበት ጊዜ ነው (ዘሌ 26:19-20)። የመሳፍንት ዘመን በአጠቃላይ እስራኤላውያን በተደጋጋሚ በእግዚአብሔር ላይ ሲያምፁ የነበረበት ዘመን ስለነበር፣ ይሄ የረሃብ ቅጣት መምጣቱ አያስደንቅም።

በዚህ በረሃብ ጊዜ አገራቸውን ትተው ወደ ሞዓብ (ባዕድ) ምድር መሄድ ነበረባቸው ወይ? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ነው። ምክንያቱም አንድ ችግር በመጣ ቁጥር ስፍራችንን እየለቀቅን መሄድ ሳይሆን እግዚአብሔርን እየተማፀንን መጠበቁ የሚመረጥ ነው። ችግሩ የቦታ ለውጥ ሳይሆን የልብ ለውጥ ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ግን ወደ ሞዓብ ምድር መሄዳቸው በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ያለ ይመስላል። ወደ ሞዓብ ምድር ባይሄዱ ኖሮ ሩት ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር ተማርካ (በኑኃሚን በኩል) ባልመጣች ነበር። እግዚአብሔር የሰውን ድካምና ጉድለት እንኳን ለክብሩና ለዘላለማዊ ዓላማው እንደሚጠቀምበት እናያለን። ሞዓብ የሎጥ ዘር እንደሆነ እናያለን (ዘፍ 19:37)።

ወደ ሞዓብ አገር ከሄዱ በኋላ በመጀመሪያ አቤሜሌክ ሞተ። ሁለቱ ልጆቹ መሐሎንና ኬሌዎን ከሞአባዊያን ሴቶች ሚስት አገቡ። የአንደኛዋ ስም ሩት የሌላይቱም ዖርፋ ነበር። አስር ዓመታት ያህል ከተቀመጡ በኋላ ሁለቱ ልጆችዋ ይሞታሉ፤ ኑኃሚንም ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ትቀራለች።

በሞአብ ምድር እያለች እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደጎበኘና እንጀራን እንደሰጣቸው ስትሰማ አገሯ ለመመለስ ከምራቶችዋ ጋር ተነሳች፡፡ በመንገድም እያሉ ኑኃሚን ምራቶችዋን፤ «ወደ እናቶቻችሁ ቤት ተመለሱ፤ ባልም አግብታችሁ ኑሮአችሁን ቀጥሉ፣ ለምን ከእኔ ጋር ትንከራተታላችሁ?» ትላቸዋለች፡፡ እነሱም ካለቀሱ በኋላ ከአንቺ ጋር ወደ አገርሽ እንመለሳለን ይሉአታል፡፡ እንደገና ግድ ስትላቸው ዖርፋ እሺ ብላ ኑኃሚንን በመሰናበት ወደ አገሯ ትመለሳለች፡፡

«ዖርፋም አማትዋን ሳመች ሩት ግን ተጠጋቻት» (ቁ 14)፡፡

ዖርፋ ከተመለሰች በኋላ ሩትን «እነሆ ባልንጀራሽ ወደ ሕዝብዋና ወደ አማልክትዋ ተመለሰች፤ አንቺም ደግሞ ከባልንጀራሽ ጋር ተመለሽ አለቻት፡፡» መቼም እውነተኛ የሆነ ፍቅር ምንም ዓይነት ግፊትና ፈተና ቢመጣበትም ማለፉ አይቀርምና፤ ምናልባት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከኢየሱስ ፍቅር ቀጥሎ ድንቅ የሆነ ፍቅርንና ታማኝነት የተሞላበትን ቃል ሩት ለኑኃሚን ትናገራለች፡፡

«ወደምትሄጂበት እሄዳለሁና በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል በምትሞቺበት ስፍራ እሞታለሁ በዚያም እቀበራለሁ ከሞት በቀር አንቺንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ እንዲሁም ይጨምርብኝ አለች» (ቁ 16)፡፡

«ኑኃሚንም ከእርስዋ ጋር ለመሄድ እንደ ቆረጠች ባየች ጊዜ እርስዋን ከመናገር ዝም አለች» (ቁ 18)፡፡ ወደ ቤተልሔም ከተመለሱም በኋላ የከተማይቱ ሰዎች ይህች ኑኃሚን ናትን? በማለት ይቀበሏቸዋል፡፡ «ኑኃሚን» ደስተኛ ማለት ነውና ለምን ኑኃሚን ትሉኛላችሁ ሁሉን የሚችል አምላክ አስመርሮኛልና ማራ በሉኝ ትላቸዋለች፡፡ በተጨማሪም፤ «በሙላት ወጣሁ እግዚአብሔርም ወደ ቤቴ ባዶዬን መለሰኝ» ብላ ታማርራለች፡፡

የኑኃሚንን ቃላት በምንሰማበት ጊዜ ነገሮችን የምታየው ከራስዋ ውስን ከሆነ አመለካከት እንጂ ከእግዚአብሔር ሐሳብና

ዓላማ አንፃር እንዳልሆነ እንመለከታለን፡፡ እርስዋ ያየችው ባልዋና ሁለት ልጆችዋ መሞታቸውን ብቻ ነው፡፡ መቼም አንዲት ድንቢጥ እንኳን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አትወድቅምና የባሏና የልጆችዋ መሞትም ከእግዚአብሔር ዕቅድና ዓላማ ውጭ አልነበረም፡፡

እግዚአብሔር ለኑኃሚን የነበረው ዋና ዓላማ ከሞአብ አገር ወደ እስራኤል (ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ) ሊያመጣት የፈለጋት አንዲት ዕንቁ ስለነበረች፤ ያቺን ዕንቁ አስይዞ ሊያመጣት፣ በእጅዋ ይዛ የነበረውን ሁሉ ሲያስጥላት እንመለከታለን፡፡ ኑኃሚን ግን ይህ የእግዚአብሔር ዓላማ ስላልገባት በሙላት ወጣሁ እግዚአብሔርም ወደ ቤቴ ባዶዬን መለሰኝ አለች፡፡ ብዙ ጊዜ እኛ ሙላት የምንለውን እግዚአብሔር ባዶ ይለዋል፡፡ እኛ ባዶ የምንለውን ደግሞ ሙላት ይለዋል፡፡ «አሳቤ እንደ አሳባችሁ፣ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና» ይላል (ኢሳ 55:8)፡፡

ከባዕድ ምድር ይህችን ዕንቁ የሆነች ሴት (መሲሁ በእርስዋ በኩል ሊመጣ ከዘሩ ሐረግ ውስጥ ሊያስገባት የወደዳትን ሴት) ይዛ፣ ባዶዬን መለሰኝ ትላለች፡፡ በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል እንደሚባለው የእግዚአብሔር ሐሳብ ቢገባት ኖሮ እግዚአብሔር ሆይ! የደረሰብኝ ምሬትና ጭንቀት ሁሉ ለመልካም ስለሆነ አመሰግንሃለሁ ባለች ነበረ፡፡

## የሩት ትጋትና ትሕትና (ሩት ምዕ 2)

ወደ ቤተልሔም ከአማትዋ ጋር እንደተመለሰች ወዲያውኑ ወደ እርሻ ሄዳ ለመቃረም ፈቃድን ከአማትዋ ስትጠይቅ እናያለን፡፡ መቃረም ማለት ሌላው ትቶ ወይንም ሳይለቅም ረስቶ የሄደውን እህል መልቀም እንደመሆኑ መጠን በሰዎች ዘንድ የተናቀና ወደታች የሚታይ ሥራ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ሩት በትሕትና ዝቅ ብላ ይህንን ሥራ <u>በትጋት</u> ትሠራለች፡፡ ከአጫጆቹ አንዱ ስለ እርስዋ ሲናገር «ከማለዳም ጀምራ እስከ አሁን ድርስ ቆይታለች፤ በቤትም ጥቂት ጊዜ እንኳን አላረፈችም» (ቁ.7) ብሎ ይመሰክራል፡፡

በተጨማሪ፤ በዚህ ምዕራፍ የአቤሜሌክ ዘመድ የሆነውን በእስራኤል ባህል ደግሞ ሩትን ሊቤዥ የሚችለውን ቦኤዝ የተባለ የእግዚአብሔር ሰው እናያለን።

በሰው በኩል አጋጣሚ፤ በእግዚአብሔር በኩል ግን በሰማያዊ እቅድ፣ ሩት በዚህ ሰው እርሻ ለመቃረም ትመጣና ይህ ሰው ስለማንነትዋ ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ለኑኃሚን ስላደረገችው ቸርነት ያመሰግናታል። በእግዚአብሔር ስምም እንዲህ ብሎ ይባርካታል፤ «እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ፣ ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኚ በመጣሽበት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ ደመወዝሽ ፍጹም ይሁን» (ቁ. 12)። ይህ ባርኮት፣ ሩት ወደ ቤተልሔም የመጣችው ኑኃሚንን ብቻ ፈልጋ ሳይሆን የኑኃሚንና የእስራኤል አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን ፈልጋ እንደነበር ያሳያል።

ኑኃሚን ምንም በሁኔታው ብትመረርና ብትጨነቅም ለሩት ጥሩ ምስክር ሆናላት እንደነበረ ማየት እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ለእኛ በማይመች ሁኔታ ውስጥ እያለፍን እንኳን ለሌሎች ሕያው እግዚአብሔርን ማሳየት አለብን።

## የሩት ታዛዥነት (ሩት ምዕ. 3)

ምንም እንኳን ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ ብትሆንም፤ የአገሩን ባህልም በደንብ ባታውቅ፤ ኑኃሚን የምትነግራትን ነገር ሁሉ ስትታዘዝ እናያለን። ኑኃሚንም ለሩት ያላት ሐሳብና ምኞት ቅን ስለነበር እንዲህ ትላታለች፤ «ልጄ ሆይ! መልካም እንዲሆንልሽ ዕረፍት አልፈልግሽምን?» (ቁ1)።

ከዚህ ቀጥሎ የምትሰጣት ትእዛዝ በሞተው ባሏ ፋንታ ሆኖ እርሷን በማግባት የሟቹንም ስም ሆነ የእርሷን ስም ሊያስጠራ የሚችለው ሰው ቦኤዝ ስለነበረ ወደዚህ ሰው ተጠግታ እግዚአብሔር ያዘጋጀላትን በረከት እንድትቀበል የሚያሳስብ ነበር።

በአጭሩ አነጋገር ለትዳር እንድትጠይቀው ትነግራታለች። ሩትም አማትዋ ያዘዘቻትን ሁሉ አደረገች (ቁ6)። ሩት በዚህ

ምዕራፍ በኑኃሚን ትእዛዝ የምታደርገውን ድርጊት በዘዳ 25:5-10 ላይ ከተጻፈው መመሪያ ጋር በአንድነት መመልከት ያስፈልጋል። ዋርሳዬ ነህ የምትለው በዚህ ክፍል መሠረት ነው።

ቦኤዝ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ስለነበረ ሁሉንም በሥርዐቱ ሲያደርግ እናያለን። ከእኔ ይልቅ ለአቤሜሌክ የሚቀርብ ሰው ስላለ በመጀመሪያ እርሱ ዋርሳ መሆን ይወድድ እንደሆነ እጠይቀዋለሁ፤ እርሱ እምቢ ካለ እኔ ዋርሳ እሆንሻላሁ በማለት ቃል ይገባላታል። የሩት እርምጃ እዚህ ላይ ሲያበቃ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ኃላፊነት የቦኤዝ እንደሆነ እናያለን።

«ደሞዝሽ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ይሁን» ብሎ እንደባረካት (ምዕ. 2፡12) እግዚአብሔር ደሞዝዋን በእርሱ በራሱ በኩል ሲያዘጋጅላት እናያለን።

ኑኃሚንም ይህንን ሁሉ ስትሰማ ልጄ ሆይ ሰውየው ይህን ነገር ዛሬ እስኪጨርስ ድረስ አያርፍምና ፍጻሜው እስኪታወቅ ድረስ ዝም በይ (ቁ 18) ትላታለች።

## የሩት ደሞዝና ዋጋ (ምዕ 4)

ሩት ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም የሆነ ደሞዝን ትቀበላለች።

ሊቤዠት የሚችለውና ቃል የገባላት ቦኤዝ እንደተናገረው ከእርሱ ይልቅ በዝምድና የሚቀርባቸውን ሰው በከተማይቱ በር አደባባይ ስላገኘው በሽማግሌዎች ፊት የአቤሜሌክን ርስት እንዲቤዥ ሲጠይቀው፤ ይህ ሰው እቤዠዋለሁ በማለት ይመልሳል። ነገር ግን ከርስቱ ጋር አብሮ የሟቹን ማለትም የሩትን ባል ስም እንዲያስነሳ፣ ሩትንም መውሰድ (መቤዠት) እንዳለበት ሲነግረው አሕዛብ (ሞአባዊት) እንደሆነች ስለሚያውቅ ሳይሆን አይቀርም፤ «የራሴን ርስት እንዳላበላሽ መቤዠት አልችልም፤ እኔ መቤዠት አልችልምና አንተ ከእኔ መቤዠቱን ውሰደው» ይለዋል (ቁ. 6)። ርስቴ ለአሕዛብ እንዳይሆን ማለቱ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ይህችን ሴት ምን ያህል እንዳከበራት ቢገባው ኖሮ መሬት ስሞ ይቀበል ነበር።

ቦኤዝም በሽማግሌዎቹ ሁሉ «ፊት የሚቹን ስም እንዳላበላሽ ርስቱ ላይ እንዳስነሳ የመሐሎንን ሚስት ሞአባዊቱን ሩትን ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ወሰድኳት» (ቁ 10)፤ በማለት ሩትን ሚስቱ አድርጐ ይወስዳታል። እነዚህም ምስክሮች «እግዚአብሔር ይህችን ወደ ቤትህ የምትገባውን ሴት የእስራኤልን ቤት እንደሠሩ እንደ ሁለቱ እንደ ራሄልና እንደ ልያ ያድርጋት» በማለት ድንቅ በሆነ ባርኮት ይባርኩታል።

በእውነትም ይህ ባርኮት ድንቅ ነው፤ ምክንያቱም ራሄልና ልያ የእስራኤልን ነገድ እንደሠሩ ሁሉ ሩትም የዳዊትን፣ ከዚያም መሲሁ የሚመጣበትን ቤት ሠራች። ከሩት የተወለደው ልጅ ኢዮቤድ ተባለ፤ እርሱም የዳዊት አባት የእሴይ አባት ሆነ። ኑኃሚንም «እግዚአብሔር አስመርሮኛል» እንዳለችው ሳይሆን በመጨረሻ ላይ እግዚአብሔር ደስ ሲያሰኛት እናያለን። «ኑኃሚንም ሕፃኑን ወሰደች አቀፈችውም ሞግዚትም ሆነችው» (ቁ. 14-16)።

## <u>በመጽሐፈ ሩት የሚገኙ ምሳሌያዊ ነገሮች፤</u>

**<u>ሩት</u>**፤ የአሕዛብ በክርስቶስ አካል (በቤተ ክርስትያን) ውስጥ የመግባት ምሳሌ ነች።

«እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ።» (1ጴጥ 2:10)

**<u>ቦኤዝ</u>**፤ የክርስቶስ ኢየሱስ ምሳሌ ነው።

ቦኤዝ ሩትን እንደተቤዠ፤ እኛንም ኢየሱስ ክርስቶስ ተቤዠን፣ ዋጀን።

<u>ኑኃሚን</u>፤ ከግል ሰብአዊ አመለካከቷ ሌላ፣

ሩትን ከቦኤዝ ጋር ማገናኘቷና ሩትን ትክክለኛ ምሪት በመስጠትዋ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደሚመራንና እንደሚያቀርበን የምታሳይ ምሳሌ አድርገን ልናያት እንችላለን።

ሩትን መቤዠት አልችልም ያለው ሰው፤

ወደ እግዚአብሔር ጽድቅ ሊያደርሰን የማይችለውን ሕግን ይመስላል፡፡
«ከሰው ባህርይ ደካማነት የተነሳ ሕግ ሊያደርገው ያልቻለውን እግዚአብሔር አድርጎታል፡፡ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ ላከ፤ ለኃጢአት መስዋዕት ባደረገውም በዚሁ በልጁ ሥጋ የሰውን ኃጢአት በፍርድ አስውግዶአል» (ሮሜ 8፥3)፡፡

«በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል፡፡» ገላ 5:4፡፡ በሕግ በኩል ቢሆን ሩት ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ለመቀላቀል ጭራሽ አትችልም ነበር፤ ምክንያቱም ሕጉ እንዲህ ይላል፡፡

«አሞናዊና ሞዓባዊ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ እስከ 10 ትውልድ ድረስ ለዘላለም ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ» (ዘዳ 23:4)፡፡ ነገር ግን ሩት በሕጉ በኩል ሳይሆን እግዚአብሔር ባዘጋጀላት ቤዛ በኩል ወደ እግዚአብሔር ጉባኤና ወደ መሲሁ የትውልድ ሐረግ ገባች፡፡

የህግ ምሳሌ ለሆነው ለዚህ ሰው ያልተቻለውን መቤዠት፤ የየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ቦኤዝ ሲያደርገው (ሩትን ሲቤዠት) እናያለን፡፡


*Global Good News Literature*

*P.O.Box 451336*

*Los Angeles, CA 90045*


(C) Copyright 2013